# ጳውሎስ - ከአሳዳጅነት ወደ ክርስቶስ ሃዋርያነት

ስም፡-________________________________________________

ከተማ፡_______________________________________________

1. የሐዋርያው ጳውሎስ የአይሁድነት ሥሙ ማን ይባላል?

   ሀ. ኤርሚያስ ለ. ጌዴዮን ሐ. ሳዖል መ. አቤሴሎም

2. የጳውሎስ ነገድ

   ሀ. ዳን ለ.ቢንያም ሐ.ይሁዳ መ.ይሳኮር

3. ጳውሎስ የተወለደባት ከተማ

   ሀ.ሮም ለ. አንጾኪያ ሐ. አቴንስ መ. ተርሴስ

4. የጳውሎስ የእህት ልጅ የሚኖርበት ከተማ

   ሀ. ተርሴስ ለ. ቀርጤስ ሐ. ኢየሩሳሌም መ.ኢያሪኮ

5. የጳውሎስ አባት ይከተለው የነበረው እምነት

   ሀ. የፐሌቶን ለ. የኢየሱስን ሐ. ስቶሲዝም መ. ፈሪሳዊነት

6. የጳውሎስ ዜግነት

   ሀ. ግሪካዊ ለ.ፍልስጤማዊ ሐ. ሮማዊ መ.ደማስቆዊ

7. ጳውሎስን ያስተማረው ሊቅ

   ሀ.ገማልያ ለ.ሂላል ሐ.አውግስጦስ መ.ሄሮድ

8. ይህ አማኝ ሲገደል ጳውሎስ ቆሞ ይመለከት ነበር

   ሀ.ይሁዳ ለ.በርባን ሐ.ሃናንያ መ.እስጢፋኖስ

9. ጳውሎስ በዚህ ከተማ ያሉትን አማኞችን አስሮ ወደ ወህኒ ለመውሰድ ከኢየሩሳሌም ስልጣን ተቀብሎ ነበር።

   ሀ.አንጾኪያ ለ.ባቢሎን ሐ.ደማስቆ መ. ጢሮስ

10. በቀትር በመንገድ ላይ ሳለ ጳውሎስ ከ______ጋር ተገናኘ

    ሀ.ሄሮድ ለ. ኢየሱስ ሐ.ጴጥሮስ መ.ጲላጦስ

11. ከዚህ ግንኙነት በኋላ ጳውሎስ ምን ሆነ?

    ሀ. ታወረ ለ.ገነነ ሐ. ተላላጠ መ.ታመመ

12. በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ የጻፋቸው መልዕክቶች ቁጥር

    ሀ.13 ለ.15 ሐ.17 መ. 12

©pastor Asfaw Bekele

13. ጳውሎስ በወህኒ ሳለ የጻፈው ደብዳቤ

ሀ. 1 ተሰሎንቄ ለ. 1 ጢሞቲዎስ ሐ.ኤፌሶን መ.ቲቶ

14. የጳውሎስ የዕጅ ሞያ

ሀ. ሰዓሊ ለ.አሳ አጥማጅ ሐ.መርከበኛ መ.ድንኳን ሰፊ

15. ሐዋርያ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. የተቀባ ለ.የተሾመ ሐ.የተላከ መ.የተጠራ

16. ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ______ ነበር

ሀ. የቤ.ክ አሳዳጅ ለ.የቤ.ክ. ሰማዕት ሐ. ጸሐፊ መ.ሰባኪ

17. ጳውሎስ በይሁዳ ቤት ሳይበላና ሳይጠጣ ምን ያህል ጊዜ ቆየ?

ሀ.1 ቀን. ለ. 3 ቀን. ሐ. 1ሳምንት መ. 2 ቀን.

18. ጳውሎስ እንዲፈወስ እግዚአብሔር የላከው ሰው

ሀ.ሃናንያ ለ.ያዕቆብ ሐ.አጵሎስ መ.ዮሃንስ ማርቆስ

19. ጳውሎስ ከተፈወሰ በኋላ ጳውሎስ ሊሰብክ ወዴት ሄደ

ሀ. ገበያ ለ.ቤ.ክ. ሐ.ምኩራብ መ. መቅደስ

20. ጳውሎስ ከደማስቆ ያመለጠው

ሀ.በቅርጫት ለ.በፈረስ ሐ.መሰላል መ.ሠረገላ

21. ጳውሎስ ካመለጠ በኋላ ወዴት ሄደ

ሀ.የከለዳውያን ዑር ለ.ስፔን ሐ.አረቢያ መ.ግሪክ

22. ከተለወጠ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጀመሪያ ጊዜ የሄደው ማንን ለመጎብኘት ነበር?

ሀ. ዮሐንስን ለ.ጴጥሮስ ሐ.ማርያም መ. ያዕቆብ

23. ጳውሎስ የተላከው ለ_______ለመስበክ ነው

ሀ. አይሁድ ለ.ሮማውያ ሐ.ሙስሊም መ.አህዛብ

24. በጳውሎስ የመጀመሪያ የወንጌል ጉዞ አብሮት ይጓዝ የነበረው ከ______ጋር ነበር።

ሀ.ጢሞቲዎስ ለ.ቆርኔሌዎስ ሐ. ሉቃስ መ.በርናባስ

©pastor Asfaw Bekele

25. በጳውሎስ የወንጌል ጉዞ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች - የሀዋርያት ሥራን ያገናዝቡ

በአንደኛ ጉዞ ከሆነ - **ሀ**፤ በሁለተኛ ጉዞ ከሆነ - **ለ**፤ በሦስተና ጉዞ ከሆነ - **ሐ** በል

_________በልስጥራ ሽባው ተፈወሰ

_________በልስጥራ ጳውሎስ በድንጋይ ተወገረ

_________ልድያ ልቧ ተከፈተ

_________ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ታሰረ

_________ጠንቋዩ ኤልማስ ተቀጠ

_________በአቲና ጳውሎስ መንፈሱ ተበሳጨበት

_________በባህር ላይ መርከብ ተሰበረባቸው

_________ጠንቋዩ በርያሱስ ታወረ

_________በቆሮንጦስ ጵርስቅላና አቂላን አገኘ

_________በወህኒ ሆኖ ደብዳቤ ጻፈ

_________ዮሃንስ ማርቆስ አገልግሎቱን አቋርጦ ወደ ቤቱ ተመለሰ

_________ዲሜጥሮስ በጳውሎስ ላይ ከፋበት

_________በማልታ ደሴት እፉኘት ነደፈችው

_________በኤፌሶን 50000 ብር የሚገመት የጥንቆላ መጽሐፍ ተጣለ

_________ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ገረዘው

_________ጳውሎስ ለቄሳር ይግባኝ አለ

26. በጳውሎስ ዘመን የታወቁት ሁለቱ የህግ መምህራን

ሀ. ገማልያና ሰላጥያ　　ለ.ሂላልና ጦብያ　　ሐ.ገማልያና ሰማርያ　　መ.ገማልያና ሂላል

27. የጳውሎስ የህግ አተረጓጓም ወደየት ያደላል?

ሀ. ወደ ሰላጥያ　　ለ.ወደ ሂላል　　ሐ.ወደ ገማልያ　　መ.ወደ ሰማርያ

28. የሚከተሉትን ***እውነት*** ወይንም ***ሃሰት*** በል

____________ሀ.ጳውሎስ ከደማስቆ ልምምዱ በኋላ የሥራ ለውጥ አድርጓል።

____________ለ.ስለደህንነት ያለው አመለካከት ተለውጦዓል።

____________ሐ.የአይሁድ አምላክና የክርስቲያን አምላክ የተለያየ መሆኑን ተረዳ።

____________መ.ብሉይ ኪዳን ራሱ በራሱን ያለአዲስ ኪዳን የሚፈጸም መሆኑን ተረድቶአል።

29. የጳውሎስ ስብከት/ትምህርት በምን ዙሪያ የሚያተኩር ነው?

ሀ. ህግንን መፈጸም　　ሐ. የክርስቶስ ሞትና ትንሳዔ
ለ. ጸጋው በነጻ መቀበል　　መ. አማኝ በክርስቶስ ብቻ መታረቁ

©pastor Asfaw Bekele

30. ከጳውሎስ ሕይወት የተማርከውን አምስት ዋና ዋና ነገሮች ፃፍ

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

31. ስለጳውሎስ ህይወት መረጃ የሚሰጡን ሁለቱ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ምንና ምን ናቸው?

ሀ. የጳውሎስ መልዕክቶችና የራዕይ　　ለ. የሐዋርያት ስራና የቆሮንቶስ መልዕክት
ሐ. የጳውሎስ መልዕክትና ፍልጵስዮስ　　ሐ. የጳውሎስ መልዕክቶችና ሐዋርያት ሥራ

32. ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ስሙ የተጠቀሰው ከምን ታሪክ ጋር በተያያዘ መልኩ ነው?

ሀ. ከበርናባስ ጋር　　ለ. ከደማስቆ ስደት ጋር
ሐ. ከእስጢፋኖስ መወገር ጋር　　መ. ከበዓለ ኃምሳ ጋር

33. የጳውሎስ ዜግነት

ሀ. እስራኤላዊ　　ለ. ሮማዊ　　ሐ. ተርሴሳዊ　　መ. ሀ እና ለ

34. ጳውሎስ እንዴት እንደተለወጠ የሚናገሩት ሦስቱ የሐዋርያት ሥራ መልዕክቶች

ሀ. ሐዋርያት ሥራ 8፤ 21፤ 25　　ለ.ሐዋርያት ሥራ 11፤ 23፤ 29
ሐ. ሐዋርያት ሥራ 9፤ 22፤ 26　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

35. ጳውሎስ የተለወጠው ወዴትኛይቱ ከተማ ሲጓዝ ነው?

ሀ. ተርሴስ　　ለ. ኢየሩሳሌም　　ሐ. ደማስቆስ　　መ. ቆሮንቶስ

36. ጳውሎስ መጀመሪያ የሰማው ድምጽ ምን የሚል ነበር?

ሀ. ሳውል ሳውል ለታላቅ አገልግሎት እፈልግሃለሁ
ለ. ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?
ሐ. ሳውል ሳውል ባሪያዬ እስጢፋኖስን ስለገደልክ እበቀልሃለሁ
መ. ሳውል ሳውል አንተ የኔ ነህ ተከተለኝ ታላቅ ሰው አደርግሃለሁ

37. ኢየሱስ ጳውሎስን ሲያገኘው ራሱን ማን ብሎ ነው ያስተዋወቀው?

ሀ. እኔ አልፋና ዖሜጋ ነኝ　　ለ. ሰባቱን መቅረዞች በእጄ የያዝኩኝ ነኝ
ሐ. የምታሳድደኝ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ　　መ. መልካም እረኛ እኔ ነኝ

38. ጳውሎስን ከዕውርነት እንዲፈወስና መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ እጅ ጭኖ የጸለየለት ሐዋርያ

ሀ. ሰፒራ　　ለ. ሐናንያ　　ሐ. በርናባስ　　መ. ሲላስ

©pastor Asfaw Bekele

39. ለጳውሎስ እጅ ጭኖ እንዲጸልይለት የተላከው ደቀመዝሙር ምን የሚል ትንቢት ተናገረ ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

40. ጳውሎስ እምነቱ ሲለወጥ አብሮ የተለወጡት ምን ምን ናቸው?

ሀ. የአስተሳሳብና የፈቃድ ለውጥ ለ. የስነ-መለኮት ለውጥ
ሐ. የሞያ ለውጥ መ. ሁሉም መልስ ነው

41. ጳውሎስ ካመነ በኋላ ወዲያውኑ ምን አደረገ?

ሀ. በደማስቆ ምኩራብ ሰበከ ለ. ከኃዋርያት ጋር ደብዳቤ ተጻጻፈ
ሐ. የውሃና የመንፈስ ቅዱስን ተቀበለ መ. ወደ እስያ ለአገልግሎት ወጣ

42. ጳውሎስና ሲላስ በየትኛው ከተማ ነው እንደ አማልክት ሊያመልኳቸው የነበረው?

ሀ.በኢቆኒየም ለ.በቆጵሮስ ሐ. በደርቤ መ. በልስጥራ

43. ጳውሎስ በድንጋይ የተወገረበት ከተማ

ሀ.በኢቆኒየም ለ.በቆጵሮስ ሐ. በደርቤ መ. በልስጥራ

44. በሁለተኛው የወንጌል ጉዞ ከጳውሎስ ጋር አብረው የተጓዙት እነማን ናቸው?

ሀ. በርናባስ፣ ሲላስና ዮሃንስ ማርቆስ ለ. ሲላስ፣ ጢሞቲዎስና ሉቃስ
ሐ. በርናባስ፣ ጢሞቲዎስና ዮሃንስ ማርቆስ መ. ቲቶ፣ ጢሞቲዎስና ቲኪቆስ

45. ለአውሮጳ የወንጌል መግቢያ በር የሆነችው ከተማ

ሀ. ኤፌሶን ለ. ፍልጵስዮስ ሐ. ቆላስይስ መ. አቴንስ

46. ከጳውሎስና ጋር አብረው ተመሳሳይ የድንኳን መስፋት ሞያ የነበራቸው ባልና ሚስት

ሀ. ሃናንያና ሰጲራ ለ. ጵርስቅላና አቂላ ሐ. ዱሪሲላና ፊልሞና መ. ሁሉም

47. ጳውሎስ መጀመሪያ የጻፈው መልዕክት

ሀ. ሮሜ ለ. ቆሮንጦስ ሐ. ነተሰሎንቄ መ. ኤፌሶን

48. ጳውሎስ ከሁለት አመት ተኩል በላይ ተቀምጦ ያገለገለበት ከተማ

ሀ. ሮሜ ለ. ቆሮንጦስ ሐ. ነተሰሎንቄ መ. ኤፌሶን

49. ጳውሎስ በባህር ላይ የመርከብ አደጋ ከተረፈ በኋላ በደሴት ላይ ሌላ የደረሰበት አደጋ

ሀ. የድንጋይ ናዳ ለ. የምግብ ማጣት ሐ. በእፉኝት መነደፍ መ. ስደት

©pastor Asfaw Bekele